# ትንቢተ አብድዩ

**የአብድዩ ራእይ፤**

1 ጌታ *እግዚአብሔር* ስለ ኤዶም እንዲህ
ይላል፤
*ከእግዚአብሔር* ዘንድ መልእክት
ሰምተናል፤
መልእክተኛውም ወደ አሕዛብ ተልኮ እንዲ
ህ
ብሎአል፤
"ተነሡ፤ እርሷን ለመውጋት እንውጣ።"
2 "እነሆ፤ በአሕዛብ መካከል ታናሽ
አደርግሃለሁ፤
እጅግ የተናቅህ ትሆናለህ።
3 አንተ በሰንጣቃ[ሀ] ዐለት ውስጥ
የምትኖር፣
መኖሪያህንም በከፍታ ስፍራ ያደረግህ፣
ለራስህም፣
'ማን ወደ ምድር ሊያወርደኝ ይችላል?'
የምትል፣
የልብህ ትዕቢት አታልሎሃል።
4 እንደ ንስር መጥቀህ ወደ ላይ ብትወጣ፣
ጎጆህንም በከዋክብት መካከል
ብታደርግ፣
ከዚያ አወርድሃለሁ"
ይላል *እግዚአብሔር*።
5 "ሌቦች ወደ አንተ ቢመጡ፣
ዘራፊዎችም በሌሊት ቢገቡ፣
የሚሰርቁት የሚፈልጉትን ያህል
ብቻ አይደለምን?
ወይን ለቃሚዎች ወደ አንተ ቢመጡ፣
ጥቂት ቃርሚያ አይተዉምን?
አንተ ግን ምንኛ ጥፋት ይጠብቅሃል!
6 ዔሳው ግን እንዴት ተዘረፈ?
የሸሸገውስ ሀብት ምንኛ ተመዘበረ!
7 ወዳጆችህ ሁሉ ወደ ድንበር ይገፉሃል፤
ጓደኞችህ ያታልሉሃል፤ ያሸንፉህማል፤
እንጀራህን የበሉ ወጥመድ ይዘረጉብሃል፤[ለ]
አንተ ግን አታውቀውም።
8 "በዚያ ቀን ጥበበኛ ሰዎችን ከኤዶም፣
አስተዋዮችንም ከዔሳው ተራሮች
አልደመ
ስስምን?"
ይላል *እግዚአብሔር* ።
9 ቴማን ሆይ፤ ተዋጊዎችህ ይደነግጣሉ፤
በዔሳውም ተራሮች ያለ ሁሉ፣
ተገድሎ ይጠፋል።
10 በወንድምህ በያዕቆብ ላይ ስላደረግኸው
ግፍ፣
በዕፍረት ትሸፈናለህ፤
ለዘላለምም ትጠፋለህ።

11 እንግዶች ሀብቱን ዘርፈው ሲሄዱ፣
ባዕዳንም በበሮቹ ሲገቡ፣
በኢየሩሳሌምም ላይ ዕጣ ሲጣጣሉ፣
በዚያ ቀን ገለልተኛ ሆነህ ተመለከትህ፣
አንተም ከእነርሱ እንደ አንዱ ሆንህ።
12 ክፉ ቀን በገጠመው ጊዜ፤
በወንድምህ ሥቃይ መደሰት
አልነበረብህም፤
በጥፋታቸው ቀን፣ የይሁዳ ሕዝብ ሲያዝኑ
ሐሤት ማድረግ አልነበረብህም፤
በጭንቀታቸውም ቀን፣
በትዕቢት ልትናገር አይገባህም ነበር።
13 በጥፋታቸው ቀን፣
በሕዝቤ በር መግባት የለብህም ነበር፤
በጥፋታቸው ቀን፣
በጭንቀታቸው መደሰት
አልነበረብህም፤
በጥፋታቸው ቀን፣
ሀብታቸውን መዝረፍ አይገባህም ነበር።
14 ስደተኞቻቸውን ለመግደል፣
በመንታ መንገድ መጠባበቅ አይገባህም
ነበር፣
በጭንቀታቸው ቀን፣
የተረፉትን አሳልፈህ መስጠት
አልነበረብህም።
15 "በአሕዛብ ሁሉ ላይ፣
የእግዚአብሔር ቀን ደርሶአል፤
አንት እንዳደረግኸው፣ በአንተም ላይ ይደረጋል፤
ክፉ ሥራህም በራስህ ላይ ይመለሳል።
16 እናንተ በቅዱሱ ተራራዬ እንደ
ጠጣችሁ፣
አሕዛብ ሁሉ ዘወትር ይጠጣሉ፤
ይጠጣሉ፤ አብዝተውም ይጠጣሉ፤
ከዚህም በፊት እንዳልሆኑት ይሆናሉ።
17 ነገር ግን በጽዮን ተራራ ነጻ መውጣት
ይሆናል፤
የያዕቆብ ቤትም እርሷ የተቀደሰች
ትሆናለች፤
ርስታቸውን ይወርሳሉ።
18 የያዕቆብ ቤት እሳት፣
የዮሴፍም ቤት ነበልባል ይሆናል፤
የዔሳው ቤት ገለባ ይሆናል፤
ያቃጥሉታል፤ ይበሉትማል፤
ከዔሳው ቤት የሚተርፍ፣ አይኖርም።"
*እግዚአብሔር* ተናግሮአል።
19 የኔጌብ ሰዎች፣

1፥1 ዘፍ25፥14፤ ኢሳ1፥1፤11፥14፤ 18፥2፤34፥11፤ 63፥1-6፤ኤር6፥4-5፤ 49፥7-22፤ሕዝ 25፥12-14፤32፥29፤ አሞ1፥11-12
1፥2 ዘኊ24፥18
1፥3 2ዜና25፥11-12፤ኢሳ16፥1፥6
1፥4 ኢዮ20፥6፤ ኢሳ10፥14፤14፥13
1፥5 ዘዳ4፥27፤ 24፥21፤ኢሳ24፥13
1፥7 መዝ41፥9፤ ኤር30፥14
1፥8 ኢዮ5፥12፤ ኢሳ29፥14
1፥9 ዘፍ36፥11፥34
1፥10 መዝ137፥7፤ ሕዝ25፥12-14፤ 35፥9፤ኢል3፥19፤ አሞ1፥11-12
1፥11 ኢዮ6፥27፤ ሕዝ24፥6፤አሞ1፥6
1፥12 ኢዮ31፥29፤ መዝ137፥7፤ ምሳ17፥5፤24፥17፤ ሕዝ25፥6፤35፥15፤ ሚክ4፥11፤7፥8
1፥13 ሕዝ35፥5
1፥14 1ነገ18፥4
1፥15 ኤር46፥10፤ 50፥29፤ ሕዝ30፥3፤ ኢል2፥31፤ አሞ5፥18፤ዕን2፥8
1፥16 ዘፀ15፥17፤ ኢሳ51፥17፤ ኤር25፥15፤ 49፥12፤ሰቆ4፥21-22፤ ሕዝ25፥12-14
1፥17 መዝ69፥35፤ 74፥2፤ኢሳ4፥3፤ 14፥12፤ኢል2፥32፤ አሞ9፥11-15፤ ዘካ8፥12
1፥18 ኢሳ1፥31፤ ኤር49፥10፤ ዘካ12፥6
1፥19 ዘኊ1፥36፤ ኢሳ11፥14፤ኤር31፥5

[ሀ]3 ወይም *በሴላ*
[ለ]7 የዚህ ሐረግ የዕብራይስጡ ትርጓሜ በእርግጠኝነት አይታወቅም።

የዔሳውን ተራራ ይይዛሉ፤
ከተራራው ግርጌ ያሉ ሰዎችም፣
የፍልስጥኤማውያንን ምድር ይወርሳሉ፤
የኤፍሬምንና የሰማርያንም ዕርሻ ይይዛሉ፤
ብንያምም ገለዓድን ይወርሳል።
20በከነዓን ያለው ይህ የእስራኤል ስደተኞች
ወገን፣
እስከ ሰራጵታ ያለውን ምድር
ይወርሳል፤
በሰፋራድም ያሉ የኢየሩሳሌም
ስደተኞች፣
የኔጌብን ከተሞች ይወርሳሉ።
21የዔሳውን ተራሮች ለመግዛት፣
ነጻ አውጪዎች ወደ ጽዮን ተራራ ይወጣሉ፤
መንግሥቱም የእግዚአብሔር ይሆናል።

1፥20 1ነገ17፥9-10፤ኤር33፥13፤ሉቃ4፥26
ራእ11፥15
1፥21 ዘዳ28፥29፤
መሳ3፥9፤መዝ22፥28፤
47፥9፤ 66፥4፤ዳን
2፥44፤ዘካ14፥9፥16፤ሚ
ል1፥14፤